# ስለ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ አስጊ ባህርይ የሚገመግም ቡድን የተማሪ ሪኮርዶችን ምስጢር የመጠበቅ ስምምነት

Department of Systemwide Safety and Emergency Management/
Office of Student and Family Support and Engagement
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland 20850
ሲስተም አቀፍ የደህንነት እና አስቸኳይ ሁኔታ ማኔጅመንት መምሪያ
የተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ ሰጪ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

እኔ________________________________________ የ [School Name] ስለ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ አስጊ ባህርይ ገምጋሚ ቡድን/Behavior Threat Assessment Team (BTAT)፣ አባል እንደመሆኔ መጠን፣ በስቴት ወይም በፌደራል ህግ እና በቤተሰብ የመማር መብት እና ግላዊ ገመና ደንብ፣ እንዲሁም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፖሊሲዎች እና የተግባር ሥርአቶች የሚፈቀድ ካልሆነ በስተቀር፣ በምስጢር የሚጠበቅ እና ይፋ የማይደረግ የተማሪ ሪኮርድ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለኖረኝ ይችላል።

በምስጢር የሚጠበቅ እና ይፋ የማይደረግ የተማሪ መረጃ/ኢንፎርሜሽን የሚያካትተው፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ አይገደብም፦-

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ወይም በ MCPS ውክልና የሚሠሩ ኤጀንሲዎች እና ግለሰቦች ዘንድ የሚገኙ የተማሪ ሪኮርዶች፣ ፋይሎች፣ ሠነዶች-ዶኩመንቶች፣ እና ከተማሪ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ሌሎች ቁሳቁሶች-ማቴሪያሎች።
2. ከተማሪ ጋር በቀጥታ የተገናኙ መረጃዎች-ኢንፎርሜሽን፣ በተለይም በማንኛውም መልኩ ሪኮርድ የተደረገ መረጃ-ኢንፎርሜሽን፣ በዚህ ያልተገደበ ቢሆንም፣ የእጅ ጽሑፍ፣ የታተመ፣ የኮምፒውተር ሚድያ፣ ቪድኦ ወይም ኦዲዮ ቴፕ ወይም ፊልምን ይጨምራል።
3. በጠቅላላ ሌሎች የትምህርት ሪኮርዶች እና በ BTAT ስብሰባዎች ላይ የተደረጉ የቃል ውይይት ሪኮርዶች።
4. በጠቅላላ ተማሪን የሚመለከቱ የ BTAT ውይይቶች ።

BTAT MEMBER CONSENT/የ BTAT ቡድን አባል ስምምነት

የ BTAT ግምገማ ላይ የተማሪን ገመና ለመጠበቅ፣ የ BTAT መሪን ጨምሮ ተገቢውን ጥበቃ ተግባራዊ ያደርጋል/ታደርጋለች፦-

1. ዛቻ፣ ማስፈራሪያ-የአደጋ ወይም የስጋት ምንጭ የሆነን ነገር በመገምገም/በመመርመር ምክንያት የተገኘ ምንም አይነት የወንጀል ታሪክ የያዘ መረጃ-ኢንፎርሜሽን ወይም ማንኛውንም የተማሪን ምስጢራዊ መረጃ-ኢንፎርሜሽን የያዘ መረጃ BTAT ግምገማ እንዲያደርግ ከተባለው ዓላማ በስተቀር ማንኛውም የ BTAT አባል በድጋሚ ማስረጃ መግለጽ አይኖርበ(ባ)ትም።
2. BTAT ሥራውን እንዲሠራ የተሰጠውን የተማሪ የወንጀል ድርጊት ታሪክ ሪኮርድ BTAT ማስቀመጥ/ማቆየት አይኖርበትም፣ ወይም የ BTAT አባል የሆነ(ች) ሰው ቅጂ መያዝ-ማስቀመጥ አይኖርበ(ባ)ትም።
3. የወንጀል ታሪክ መረጃ በተማሪው(ዋ) የትምህርት ማህደር ጋር አይቀመጥም ወይም FERPA, 34 CFR §99.3. ላይ እንደተገለጸው ከተማሪ የትምህርት ሪኮርድ ጋር አይያዝም።

ይህንን ምስጢር የመጠበቅ እና ለማንም ያለመግለጽ ስምምነት፣ እኔ አውቄ እና ተገንዝቤ ተስማምቻለሁ፦-

1. የተማሪን ምስጢራዊ መረጃ-ኢንፎርሜሽን የማገኘው የ BTAT አባል እንደመሆኔ የተመደብኩበትን ሥራዬን ለመሥራት ብቻ ስለሆነ፣ እና የተማሪን ምስጢራዊ መረጃ-ኢንፎርሜሽን ለማንኛውም እኔ ለምቀጠርበት ወይም ግንኙነት ለሚኖረኝ ሌላ ኤጀንሲ አላስተላልፍም/አላሳይም/አልገልጽም።
2. የተማሪን ምስጢራዊ መረጃ-ኢንፎርሜሽን ለማንኛውም ሰው በምንም ሁኔታ ከ BTAT ስብሰባ ውጪ፣ ለ MCPS ዲስሪክት አቀፍ BTAT፣ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፣ ወይም ለ MCPS ሠራተኛ ስለ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ አስጊሁኔታን በተመለከተ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ክልሆነ በስተቀር፣ አስተማማኝ በሆነ ታማኝነት ምስጥራዊ አድርጌ የመጠበቅ ግዴታ አለብኝ።
3. የተማሪ ምስጢራዊ መረጃ-ኢንፎርሜሽን የሚታተመው ለ BTAT ሥራ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው፣ እናም ምስጢራዊነቱን የመጠበቅ እና የታተሙ ሠነዶች-ዶክመንቶችን እንዲወገዱ የማድረግ ሃላፊነት-ተጠያቂነት አለብኝ።
4. ምስጢራዊነቱን የመጠበቅ ግዴታዬን ካልተወጣሁ የዲስፕሊን እርምጃ ሊያስወስድብኝ ወይም በ BTAT ያለኝን ተሳትፎ የማቋረጥ እርምጃ ሊያስወስድብኝ ይችላል።
5. የተማሪን ምስጢራዊ መረጃ-ኢንፎርሜሽን ማውጣት፣ ማሳየት፣ መግለጥ፣ መስጠት ተቀባይነት ስለማይኖረው እኔን ህጋዊ እርምጃ ሊያስወስድብኝ ይችላል።
6. ምስጢር የመጠበቅ ግዴታዬ የ BTAT አባልነት ከለቀቅሁም በኋላ እስካልተወሰነ ጊዜ ይቀጥላል።

**ፊርማ**

ስም ይጻፉ ________________________________________ ቀን_____/_____/_____

በኤሌክትሮኒክስ ሞልቼና ፊርሜ ያቀረብኩት ይህ ቅጽ በግሌ በአካል ቀርቤ እንደመፈረም የሚቆጠር እኩል ዋጋ ያለው መሆኑን ይገባኛል።

ፊርማ __________________________________ ማእረግ ________________________

ቅጂ በትምህርት ቤት ፋይል ወይም በዲስትሪክት አቀፍ BTAT ፋይል ይቀመጣል።